ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 5 መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

# <u>"ድል!" ማለት</u>

(ድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://youtu.be/M70lhyf7lzk)

አዲሱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ቃለ መሃላ ሲያደርጉ ለፓርላማውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰውን ሀገራዊና ሕዝባዊ መልዕክታቸውን መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. አስደምጠውናል። በቀጣይነት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የኢሕአዴግ ሊቀመንበር በመሆን አመራሩን የተረከቡት ዶክተር ዐቢይ "ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር" በማለት አድምቀው በአደረጉት ንግግር "አዲስ ምዕራፍ የምንጀምርበት አዲስ ታሪካዊ ዕድል ነው" ብለውታል።

ዶክተር ዐቢይ በኢሕአዴግ 27 ዓመት አገዛዝ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ማለት ይቻላል ኢትዮጵያን አድምቀውና አስውበው አስቀምጠዋታል። "ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ክብሯ እንድትመለስ. . ." ብለውናል። በስም ባይጠቅሷቸውም በመተማ ዓፄ ዮሐንስን፣ በአድዋ ዓፄ ምንሊክን፣ የማይጨው አርበኞችን፣ የካራ ማራና የባድመ ሰማዕታትን ከፍተኛውን ቦታ ሰጥተዋቸዋል።

በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለተከሰተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የመፍትሄ አካል ለመሆን "ከስህተታችን ተምረን ሀገራችንን የምንክስበት ወቅት ነው" ያሉን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር (ጠ/ሚ) ይህም ጉዞ የኢሕአዴግን ሕገ-መንግሥት ተገን አድርጎ የሚቀጥል መሆኑን አስምረውበታል። ይህንንም ሲያጠናክሩ እንዲህ ብለውናል፦

"...ይህ የሥልጣን ሽግግር. . .በሀገራችን ዘላቂ የተረጋጋና ሁሉን አቀፍ የሕገ-መንግስታዊ ሥርዓት መሠረት ስለመጣላችን ማሳያ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር እኩል የሚጓዝና በሕዝብ ፍላጎት የሚገዛ ህዝብን አለቃው አድርጎ የሚያገለግል ሥርዓት እየገነባን መሆኑን ያመላክታል።...መሪ ድርጅታችን ኢሕአዴግ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንገዱን አጥብቆ በመያዝ ሀገራችንን ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ በአስተዳደረበት ወቅት በሁሉም መስክ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ሕገ-መንግስታዊና ፌደራላዊ ሥርዓት ገንብቷል።..." የጥቅሱ መጨረሻ።

በጠ/ሚ መልዕክት በአብዛኛው ማራኪ ንግግር ሰምተን ታሪክ እራሱን እንዳይደግም መጠንቀቅ ይኖርብናል። በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ወቅት ሙሉ በሙሉ የተሸነፈው ወያኔ ለድርድርና ለዕርቅ እሺታን በማሳየት ሊጠራ የታሰበውን "የሙት ቀን አድማ" ባሰረዘ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የወቅቱ ጠቅላይ ሚንስትር የክህደት ድምጻቸውን አሰሙ። የሚፈልጉት ተሳክቶላቸዋልና ከዚያ በኋላ የነበሩትን ተፎካካሪ ድርጅት አመራሮችን እየለቀሙ ወደ እስር ቢከቷቸው ማን ከልካይ፣ ማን ሃይ ባይ ተገኝቶ። ወያኔ ሲበለጥ አይቸኩልም፤ አድፍጦና አድብቶ ተቀናቃኙን ከመምታት ግና አይመለስም። በመሆኑም ወጣቱ ጠ/ሚ ይህንን የወያኔ/ህወሓት ባህሪ በሚገባ ይገነዘቡት ዘንድ እናሳስባለን።

የአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ለዚህ ስልጣን መመረጥ የህወሓት የሽንፈት ምልክት ሲሆን በመላው ሀገሪቷ ይህንን ሥርዓት ለመጣል የታገሉ ኢትዮጵያውያን የትግል ውጤት ነው እንላለን። ከህወሓት የኢሕአዴግ ምክር ቤት አባላት አንድም ድምጽ ያላገኙት ዶር ዐቢይ የኦብዴድና የብአዴን እንዲሁም የደቡብ ሕዝቦች ወኪሎች ድምጽ ለመመረጥ አብቅቷቸዋል። ለ27 ዓመት የሥልጣን እርከኑን ማዕከል አድርጎ ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ በመሆን የገዛው ህወሓት/ወያኔ ዛሬ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን አብረውት ያሉት አጋሮቹ እየሸሹት ያሉ ይመስላል። ዛሬ ከህወሓት አባላት በቀር ወያኔ በኢሕአዴግ ስም ያሰባሰባቸው አጋር ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት እንደበፊቱ ትዕዛዝ ተቀባይ አለመሆናቸውን በአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር መመረጥ ተንጸባርቋል። በተመሳሳይ ሁኔታ አጋር የህወሓት ድርጅቶች የተከሰተው ሂደት በቀጣይነት ያለ አንዳች ፍራቻ ኃይላቸውን ከአዲሱ ጠ/ሚ ጋር ከአደረጉ የወያኔን ማድባት ሊቋቋሙት ይችላሉ። ጠ/ሚ በንግግራቸው እንዳሰሙት ከፊታቸው የተደቀነውን የሕዝብ ጥያቄ ለመፍታት ዡሪያቸውን ሕዝብ ከቧቸዋልና ይህንን ዕድል ሳያወላውሉ ተጠቅመውበት ታሪክ ሊሠሩ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

በመጀመሪያው ታሪካዊ ንግግራቸው ዶር ዐቢይ ከታች የተቀመጡትን ማንሳት የነበረባቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ጨምረው ቢሆን ስለ ወደፊቱ ቀጣይ ሂደት ፍንጭ ይሰጡን ነበር። በተጨማሪም በህወሓት ላይ የመጡና የማያወላውሉ የሕዝብና የኢትዮጵያ መከታ ያስብላቸው ነበር። መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄ የጠቅላይ ሚንስትር መቀያየር እንዳልሆነ ለማሳየትና ቢያንስ ይህ ሹመት ይበልጥ ተስፋ ሰጭ እንዲሆን ሕዝብ እየጠየቀ ካለው ጥያቄ መካተት የነበረባቸው፦

1. ሀገርና ሕዝብ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወታደራዊ ዕዝ ሥር ወድቃ ስለ ልማትና መታደስ፣ ስለ ዴሞክራሲያዊ መብት አይወራም፣ አይታሰብም። ቅድሚያ መነሳት ያለበት ጥያቄ ነው።
2. በመላ የሀገሪቷ እስር ቤትና የወያኔ ማጎሪያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ፣ የህሊና፣ ዘርንና ሃይማኖትን ተገን ተደርጎ የታሠሩ እስረኞች በሙሉ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታትና የፖለቲካ እሥር ቤቶች መዘጋት የቤተሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን የሀገርና ሕዝብ ጥያቄ ነው።
3. በሀገራችን ሰላም ሰፍኖ የዜግነት መብት የተከበረባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን እንድትሆን ካስፈለገ ማንንም ሳያገል በሀገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን አካቶ ብሔራዊ ዕርቅ በማድረግ የጋራ ሽግግር መንግሥት የሚመሠረትበት ጉዳይ ዋናውና አስፈላጊው ነው።

ጠቅላይ ሚንስትሩ እነዚህን ጉዳዮች “እፈጽማለሁ” ባይሉ እንኳ “ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት አደርጋለሁ” ቢሉ ምንኛ ንግግራቸውን ባደመቀላቸው። እውን ሹመት ይዳብር ባልናቸው። “አሁን አልቸኩል የሚንስትሮች ምክር ቤቱን ካቋቋምሁ በኋላ አደርገዋለሁ” ብለው ከሆነ የምናየው ጉዳይ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለ27 ዓመት የመረረው አገዛዝ ይወገድለት ዘንድ ነው ሕይወቱን እየገበረ ያለው። በተለይ ለአለፉት ሦስት ዓመት ህወሓት/ወያኔን ወጥሮ የያዘውና መውደቂያው አፋፍ ላይ ያደረሰው ለጥገና ለውጥ አይደለም። የተነቃነቀ ጥርስ እንዲሉ የሥርዓት ለውጥ ይፈልጋል። ህወሓት በተናጠል፤ ኢሕአዴግ በጋራ አመራሩና ሥርዓቱ በውስብስብ ቢሮክራሲና ሙስና ከላይ እስከታች ተበላሽቷል። በጥቅሉ በፖለቲካው፣ ኢኮኖሚውና ማህበራዊ ሕይወት ኢሕአዴግ/ህወሓት ሀገሪቷ ከማትወጣበት አዘቅት በመክተቱ ልትነሳና ትንሳዬዋን ልታይ የምትችለው ኢሕአዴግን በመጠገን ሳይሆን ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ባካተተ መልኩ ለአዲስ ሥርዓት ልምላሜ መሸጋገሪያ መንግሥት ተግባራዊ ሲሆን ነው ብለን እናምናለን።

*የሥርዓት ለውጥ ስንል እንደ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” የህወሓት/ወያኔ ሕገ-መንግሥት መለወጥ አለበት ማለታችን ነው። ይህንን ከፋፋይና ዘረኛ ሕገ-መንግሥት ይዞ የሕዝብንና የሀገርን ጥያቄ መመለስ አይቻልምና። የዚህ ሕገ-መንግሥትና ሥርዓት ማብቃት ማለት የህወሓት/ወያኔ ሥርዓት ማብቃት ማለት ነው። ይህ ሥርዓት ሲያበቃለት ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ያበቃለታል። ይህ ሥርዓት ሲያበቃለት በኢትዮጵያ ገደብ የሌለው የዜግነት መብት ተግባራዊ ይሆናል። የዚህ ጊዜ በፖለቲካ አቋሙ ወደ እስር የሚወረወር፣ የሚሰደድ፣ የሚደበደብ፣ የሚገደል ጨርሶ አይኖርም። የዚህ ጊዜ ሥልጣንን መከታ አድርጎ የሕዝብና የሀገር ሀብት ዘረፋ አይኖርም። እነኚህ መሠረታዊ ጉዳዮች ተግባራዊ ሲሆኑ ሕዝባችን ወደ ልማት የሚያደርገውን ጉዞ በደስታ ይያያዘዋል፣ ባይበላም እንኳን በመብቱ ጠግቦ ያድራል። ተስፋ እየቆረጡ በአልባሌው ቦታ የዋሉ ልጆቹ በሀገር ለሀገር ይነሳሉ። በመላው ዓለም የተበተኑ ዜጎቻችን ኢትዮጵያችን ብለው ይሰባሰባሉ። ይህ እንዲሆን ነው ለዘመናት ትግል ሕይወት የቀጠፈው። ሀገር ለልጆቿ ትሆን ዘንድ ነው ደም የሚፈሰው፣ አጥንት የሚከሰከሰው።*

*አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር እንደ አንደበተ ርዕቱነታቸው፣ እንደ ምሁርነታቸው በድፍረትና በቆራጥነት ትግሉን ለመምራት ዝግጁነት ይጠበቅባቸዋል። በህወሓት/ወያኔ ሳይደለሉ የኢትዮጵያን አፈር ለመከናነብ ከተዘጋጁ በንግግራቸው እንዳነሷቸው ጀግኖች ስማቸው ዘላለማዊ ይሆናል። በተቃራኒው እንደ በፊቱ ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በወያኔ ዱላ እየተቀጠቀጡ አንገታቸውን ከደፉ የወደዳቸውን ሕዝብ እንደሚያጡ ማንም ሊነግራቸው አይገባም። ትግሉ ተፋፍሟልና ጉልበታቸው ሊዝል፣ አንደበታቸው ሊሰንፍ፣ ወኔአቸው ሊከዳ አይገባውም። ከህወሓት/ወያኔ ጠባብ ቡድን በቀር መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎናቸው ነውና ይህን ሕዝብ እንዳያሳፍሩት፣ እንዳያሸማቅቁት ሊፈተኑ እነሆ! ቤተ መንግስት ገብተዋል። ጊዜና ፋታ የማይሰጥ ሕዝባዊና ሀገራዊ ጥያቄ ከፊትዎ ተደቅኗል። “በሂደት” የሚባል ተረት ተረት እንዳይደግሙልን። 27 ዓመት ሙሉ ያሾፈው የህወሓት/ወያኔ ሂደት ይበቃናል። የኦሮሞ፣ የአማራው፣ የጋምቤላው፣ የሲዳማው፣ የኡጋዴን፣ የጉራጌው፣ የአፋሩ፣ ወዘተ ሕዝብ ጩኸትና ሕይወት ነው እርሶን ከፍ ያደረገው። መቀመጫው አጣብቆ እንዳይዞት ሀሳባችንን እንገልጻለን። እርሶን ተገን አድርጎ ድል በር ላይ የቆመውን ሕዝብ እንዳያሳፍሩት። በንግግርዎ ኢትዮጵያችን ብለው ያደመቋትን ሀገራችንን ሉዓላዊነቷ ሳይናጋ የህዝቧ አንድነት እንደተጠበቀ ለሕዝብ ያደረጓት ጊዜ እውንም ሰላማዊ ሽግግር አደረጉ።*

### *ለህወሓት/ወያኔ አመራር አካላትና አባላት*

ከሕዝብና ከሀገር በላይ ማንም የለም። ዛሬ ሕዝብ አመራራችሁንና ሥርዓታችሁን የጠላው ልጅ ወልዶ፣ አስተምሮና ድሮ የልጅ ልጅ በሚያይበት 27 ዓመት ዛሬም የምታወሩት ስለ ሙስና፣ ስለ ብልሹ አስተዳደር፣ ስለ መዝቀጣችሁና መበስበሳችሁ ነው። ይህ መላ ሀገሪቷንና ሀብቷን ተቆጣጥራችሁ በዚህ 27 ዓመት ሕዝባችንን ያሸከማችሁት ድህነትና ቅጥ ያጣ መብት ጥሰት ነው በሕዝብ ትጠሉ ዘንድ ምክንያት የሆነው። የአገዛዝ ሥርዓታችሁ ተጠልቷል። ዛሬ ዓለም ተለውጣለች፤ በጉልበትና በኃይል ተጠቅመን “እኔ ከሞትኩ . . .” እንተገብራለን የምትሉትን ቅዠት ወደ ጎን አድርጋችሁ በአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር አማካይነት ያገኛችሁትን ዕድል ተጠቅማችሁ ሀገራችሁንና ሕዝባችሁን ይቅርታ ጠይቁ። ሀገርም ሕዝብም ዘላለማዊ ናቸውና አጥፍታችሁ አትዘልቁትም። እምቢኝ ላለ ሕዝብ እሺታን ስጡት። የጠ/ሚ ዐብይን ኢትዮጵያዊነት ንግግር ቁጭ ብላችሁ እንዳደመጣችሁ ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ካደመጣችሁ እናንተንም በሚፈልገው አዲስ ሥርዓት ይቅር ይላችኋልና አስቡበት። ዛሬ እናንተን ወጥሮ የያዘው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ

እንደሆነ ተረዱት። በዘር፣ በቋንቋ አትከፋፍሉን፣ በሃይማኖት አትለያዩን ብሎ በአንድነት ተነስቷል። መጠላታችሁን በእልህና በጉልበት እናስወግዳለን ብላችሁ ተስፋ አታድርጉ። የመጨረሻው ጥፋት ሁላችንንም ይጎዳልና ከኢትዮጵያ ሀገራችሁና ከሕዝባችን ጋር ለዕርቅ በራችሁን ከፍታችሁ ሥልጣኑን አስረክቡት። በተለያዩ መንግስታት የደረሰበትን በደል ችሎ "ይቅር ለእግዚአብሔር" እያለ የኖረው ሕዝባችን ቂም በቀለኛ አለመሆኑን እንኳን ለእናንተ ለወራሪ ጠላት አሳይቷል። በእጁ የማረከውን ጠላቱን አብልቶና አጠጥቶ፣ ጋብዞ ወደ መጣበት በክብር የላከ አኩሪና ጨዋ ሕዝባችንን በአገኛችሁት በዚህ የመጨረሻ አጋጣሚ ማስደሰቱ ጠቀሜታው ከማንም በላይ ለራሳችሁ ነውና ይህን ዕድል ተጠቀሙበት እንላለን።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

የራስህና የልጆችህ የትግል ፍሬ ውጤት ነው ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ያደረጉት ዶር ዐቢይ አሕመድን ጠቅላይ ሚንስትር ያስደረገው። ዋናው ድል ግን ሀገር ያንተ ስትሆን ነው። በዚህ አዲስ ሹመት በመዘናጋት ለአፍታም ከተያያዝከው ፀረ-ህወሓት/ወያኔ ትግል ወደ ኋላ ማለት አይደለም ቆም ብሎ ለህወሓት/ወያኔ ጊዜ መስጠት አግባብ አይደለም። 27 ዓመት እምነትህ ያስተማረህና ያሳየህ ቢኖር የህወሓት/ወያኔ ዓይን ያወጣ ክህደትና ቅጥፈት ነው። ያሸነፍከውን አገዛዝ በምንም መልኩ እንዳታቅፈው፣ ጊዜ ጠባቂ ነውና እንዳታምነው። በምታደርገው ያላሰለሰ ሕዝባዊ ተጋድሎ ህወሓት/ወያኔ ተሸንፎ ሀገርህን ያንተ እስክታደርግ ድረስ ትግሉ ከቶም መቀዝቀዝ የለበትም። ***ድል ማለት*** ላንተ የዜግነት መብትህን መጎናጸፍ፣ ነጻነትህን መቀዳጀት ነው። ***ድል ማለት*** ላንተ በመረጥከውና በፈለከው መንግሥት መተዳደር ነው። ***ድል ማለት*** በየእሥር ቤቱ የሚማቅቁ ልጆችህ መፈታትና የፖለቲካ እሥርቤቶች መዘጋት ነው። ***ድል ማለት*** ላንተ ዘረኝነት ተወግዶ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት አብቦ ማየት ነው። በአጠቃላይ ***ድል ማለት*** ላንተ 27 ዓመት ጫንቃህ ላይ የተከመረው ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ነው። በመሆኑም የተጀመረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መቀጠል ይኖርበታል። በየአካባቢህና በየቂዬው አሁም የህወሓት/ወያኔ አጋዚ ጦር ምን እያደረገ እንዳለ የምታየውና የገፈቱ ቀማሽ አንተነህና ትግልህን አጠናክር ስንል ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ምክራችንን ብቻ ሳይሆን ከጎንህ መሆናችንን እናረጋግጥልሃለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!
"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"
መጋቢት 26 ቀን 2010 ዓ.ም. (April 04, 2018)

ማሳሰቢያ ፡

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin